# ለኤክስፖርት ቄራዎች የሚቀርቡ የእርድ እንስሳትን መስፈርት ለማስተዋወቅ የተዘጋጀ በራሪ ፅሑፍ

## በኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተዘጋጀ

አድራሻ፡

ስልክ፡ 0114338783

ኢሜይል፡emdidi2006@gmail.com

### አጭር መግቢያ፡

በወቅቱ ሀገራችን ወደ ውጭ ልካ የውጭ ምንዛሬ ከምታገኝባቸው ምርቶቻችን መካከል ሥጋና እርድ ተረፈ ምርት ተጠቃሽ ሲሆን ካለን የእንስሳት እርባታ እና ጤና አጠባበቅ ስርዓት ደረጃ ጋር በተያያዘ ምርቱ የሚላከው ውስን ወደ ሆኑ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ነዉ፡፡ በእነዚህ ሀገራትም ምርቱን የምንሸጠዉ ብቸኛ አቅራቢ በመሆን ሳይሆን ከበርካታ ሀገራት የሥጋ ምርታቸዉን የሚሸጡ ተሳታፊዎች ባሉበት ገበያ ዉስጥ ነዉ፡፡ ከተሳታፊዎችም በተጨማሪ ከላይ በተገለፀዉ አግባብ በእነዚህ ሀገራት ያሉ የሥጋ ምርት ተጠቃሚዎች የራሳቸዉን መስፈርት ያላቸዉ ስለሆነ በቀጣይ በእንስሳት ሀብት ልማቱ እና ጤና አጠባበቅ ስርዓቱ እየተከናወኑ የሚገኙ እና ተጨማሪ ገበያዎችን ለማስፋት የሚያስችሉ መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጡ ስራዎች እስከሚጠናቀቁ በወቅቱ ባሉ ውስን ገበያዎች ዉስጥ ለመቆየት ብቸኛ አማራጭ መስፈርቱን አዉቆ ማሟላት ብቻ ነዉ፡፡

ለዚህ ነዉ ሁሉም ኤክስፖርት ቄራዎች የእርድ እንስሳትን በሚገዙበት ወቅት የራሳቸዉን መስፈርት ሳይሆን በመዳረሻ ገበያ ላይ ያላቸዉ ደንበኛ ለበርካታ ጊዜያት የሚቆዩ ናቸዉ፡፡ ይህንን በመገንዘብ ማንኛዉም ለኤክስፖርት ቄራ የቁም እንስሳትን የሚያቀርብ አካል በመስፈርቱ መሰረት ከሆነ ደንበኝነቱም ዘላቂ እንደሚሆን ከግምት ዉስጥ በማስገባት መሰራት አለበት፡፡

**ዓለማ፡** ለኤክስፖርት ቄራዎች የሚቀርቡ የእርድ እንስሳት ማሟላት ያለባቸዉን መስፈርት በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት ግንዛቤ ለማስጨበጥ ነዉ፡፡

**ተጠቃሚዎች፡** ይህንን በራሪ ፅሑፍ የእርድ እንስሳትን ለኤክስፖርት ቄራዎች የሚያቀርቡ አካላት በተለይም በግልም ይሁን በማህበር ተደራጅተዉ በዘርፉ ለሚሰማሩ ማንኛዉም አካል የሚጠቅም ይሆናል፡፡

**ማሳሰቢያ፡** ቀጥሎ የሚዘረዘሩት መስፈርቶች ዋና ዋና ሲሆኑ ሌሎች ጥቃቅን እና በድርጅቶች ደረጃ የሚኖሩትን መስፈርቶች ግን እንስሳቱን ከሚያቀርቡለት ኤክስፖርት ቄራዎች ጋር አስቀድሞ በመነጋገር ማወቅ ይቻላል፡፡

መስፈርቶችን ማሟላት እና አለማሟላትን ከመገምገም በፊት ለኤክስፖርት ቄራዎች የሚቀርቡም ሆነ ለማንኛዉም ገበያ የሚቀርቡ እንስሳት ጤንነታቸዉን ማረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጠዉ ነዉ። ስለሆነም በእያንዳንዱ ገበያ ላይ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎችን ይዞ ጤንነትን ማረጋገጥ ቢቻል ተመራጭ ሲሆን ባህላዊ ዕዉቀትንና እንስሳቶች የሚያሳዩትን ያልተለመደ ባህሪና ገፅታ በመመልከት መለየት ይቻላል። ለአብነትም፤ የፀጉር መቆም፤ ያልተለመደ የአካላት እብጠት፣ ትኩሳትና እምባ ማንባት፣ የአፍና አፍንጫ አካባቢና ከውስጥ ቁስለት፣ ተቅማጥ፣ በቆዳ ላይ ትንንሽ እባጭ መሰል ነገር መታየት፣ በሁለቱ አፍንጫ ቀዳዳዎች መካከል ያለዉ አካፋይ ዘንግ እርጥበት ካሌላዉ፤ አንገትን ወደፊት ሰገግ በማድረግ ማሳል፣ ወዘተ ምልክቶችን ለመግዛት ካሰቡት እንስሳት ላይ ከተመለከቱ ጤናማ አለመሆናቸዉን እና ምርመራ እንደሚያስፈልግ በመረዳት እነዚህን ምልክቶች ያሳዩ እንስሳት ለእርድ መቅረብ አይችሉም።

ከ 12 እስከ 24 ሰዓታት በኤክስፖርት ቄራዎች ዉስጥ በሚገኝ ማስራቢያ በረት ያለምግብ መቆየት አለባቸዉ።

**3. የእንስሳት ደህንነትን በተመለከተ**

ማንኛዉም ለኤክስፖርት ቄራዎች የሚቀርቡ እንስሳት፡

- ወደ ገበያ ለመዉሰድ በሚያጓጉዙበት ወቅት፣
- በእግር በሚነዱበት ወቅት፣
- በተሽከርካሪ ላይ በሚጫኑበት ወቅት፤
- በተሽከርካሪ ከቦታ ቦታ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት፤
- ከተሽከርካሪ ላይ በሚወርዱበት ወቅት እና

በሌሎች ማንኛም የእንስሳትን ደህንነት አደጋ ላይ በሚጥሉ ክስተቶች ሁሉ **መደንገጥ፣ መፍራት፣ መሰቃየት እና ጫና** ውስጥ መግባት የለባቸዉም። እነዚህ ድርጊቶች

- እንስሳትን ከሚያስደነግጡ እና ከሚያስፈሩ ነገሮች ለአብነትም ድምፅ፣ ጩሀት እና የሚፈሩ የዱር እንስሳት ካሉ ከእነዚህ አካባቢ ነፃ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል።
- እንሰሳቶችን ከ 8 ሰዓት በላይ የሚጓጓዙ ከሆነ አውርዶ ማሳረፍና ምግብና ውሃ መስጠት፣ አሽከርካሪው እንስሳቱን ለጉዳት እና እንግልት በሚዳርግ መልኩ ማሽከርከር የለበትም ።
- በአንድ መኪና የሚጫኑ የእንስሳት ዓይነትና የሰውነት ክብደት/ መጠናቸውን ተመሳሳይ ቢሆኑ ፤
- እንስሳትን ለመጫንም ሆነ ለማራገፍ ማማ ምን ጊዜም ዝግጁ ሆኖ መገኘት አለበት፤ የማማውም የጐን ግድግዳ እንስሳት እንዳይወድቁ ተደርጐ መሠራት ይኖርበታል።
- እንስሳትን በዱላ እየደበደቡ ወይም በጅራፍ እየገረፉ ወደ ገበያ መዉሰድ የለብንም።

በ2010 በጀት ዓመት ከሐምሌ እስከ ጥቅምት ድረስ ለኤክስፖርት ቄራዎች ከቀረቡት እንስሳት ዉስጥ 95 በመቶ ድርሻ ያለዉ ፍየል ሲሆን የበግ ፍላጎት 5 በመቶ እንዲሁም ቀረዉ 1 በመቶ ዳልጋ ከብት ነዉ። ይህ አሃዝ የሚያሳየዉ ወደፊት አማራጭ ገበያ እስካልተገኘ ድረስ አሁን ባለዉ የኤክስፖርት ቄራዎች ደንበኞች ፍላጎት ከፍተኛዉን ድርሻ የሚይዘዉ የፍየል ሥጋ ስለሆነ በዘርፉ ተደራጅተዉም ይሁን በግላቸዉ እንስሳትን ለኤክስፖርት ቄራዎች የሚያቀርቡ አካላት በዚሁ አግባብ ቢሆን የበለጠ ትርፋማ ያደርጋቸዋል።

ስለሆነም እንስሳትን ለኤክስፖርት ቄራዎች የሚያቀርቡ አከላት ግዢ ከመፈፀማቸዉ በፊት ከሚያቀርቡለት ቄራ ጋር አስቀድሞ በመነጋገር ምን ያህል ፍየል፤ በግ እና ዳልጋ ከብት እንደሚፈልጉ መነጋገር አጅግ በጣም ወሳኝ ነዉ።

## 5. የእንስሳት ፆታና ዕድሜ

## 6. እንስሳቱ የሚገኝበት የአየር ንብረት

ወደ ፊት የሚፈጠሩትን አዳዲስ ገበያዎች እና የደንበኞች ፍላጎትን ሳያካትት፤ አሁን በሥራ ላይ የሚገኙ የሀገራችን ኤክስፖርት ቄራዎች ደንበኞች የሚፈልጉት ከቆላማ የሀገሪቷ አካባቢዎች ለአብነትም ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ጉጂ፣ ባሌ ባቢሌ፣ጂማ እና ወዘተ፤ ከደቡብ ክልል ኮንሶ፣ ደቡብ አሞ ዞን፣ ሰገን ህዝቦች አከባቢ ዞን.....፣ ከአመራ ክልል ከኮንበልቻ እና ወሰል አከባቢዎች፣ ከትግራይ ክልል ሁመራ፣ አበርገሌ፣ ራያ እና መሰል አከባቢዎች፣ ከኢትዮጵ ሱማሌ፣ ከአፋር እና ሌሎች የሀገሪቷ ቆላማ አካባቢዎች ተመራጭ ናቸዉ። ይህ መስፈርት ወደ ፊት በሚገኙት አማራጭ የገበያ መዳረሻዎች እና የሥጋ ተጠቃሚ ደንበኞች መሰረት በማድረግ ሊቀየር ይችላል።

## 7. የእንስሳቱ ክብደትና የሥጋ ይዘት

***በግና ፍየል በተመለከተ:*** ለኤክስፖርት ቄራዎች የበግና ፍየል በህይወት እያሉ ከ 16 እስከ 26 ኪሎግራም ክብደት ያላቸዉ

**ዳልጋ ከብትን በተመለከተ:** አሁን ሥራ ላይ ካሉት ኤክስፖርት ቄራዎች መካከል ቁጥራቸዉ በጣት የሚቆጠሩ አነስተኛ ቁጥር ያላቸዉ የዳልጋ ከብትን በግብዓትነት ይጠቀማሉ። እነዚህም ቄራዎች በወጣትነት ዕድሜ ላይ የሚገኙ እና የስብ ክምችታቸዉ በጣም አነስተኛ የሆነ፤ ሥጋቸዉ በቀላሉ የሚታኘክ፤ ለእርሻ እና ለመሰል የጉልበት ሥራዎች ያልተጋለጡ መሆን አለባቸዉ።

በተጨማሪም በማድለቢያ ጣቢያ ዉስጥ ለረጅም ጊዜ ያልቆዩ ቢሆኑ የሚመረጥ ሲሆን ይህም ካሉት በርካታ ጥቅሞች መካከል *የመኖ ወጪን ይቀንሳል፤ ለተንከባካቢ የሚወጣዉን ወጪ ይቀንሳል፤ የመስሪያ ገንዘብን ለረጅም ጊዜ ይዞ እንዳይቆይ በማድረግ ሌሎች እንስሳትን ያለገንዘብ ችግር ለመግዛት ያግዛል፤ እንስሳዉ ከመጠን ያለፈ የስብ ክምችት እንዳይኖረዉ ይረዳል፤* በመሆኑም ለኤክስፖርት ቄራዎች በርካታ ቁጥር ያለዉን እንስሳት በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ከጥቂት እንስሳት ብዙ ከማትረፍ ይልቅ ከበርካታ እንስሳት ከፍተኛ ትርፍ እንዲገኝ

